ይህ በቋንቋ እገዛ ማግኛ ፖሊሲ፣ ከዚህ ቀደም በዚህ ጉዳይ ላይ፣ በDCPS ታውጆ የነበረውን ሁሉንም ፖሊሲ፣ ሜሞራንዳ (memoranda)፣ እና/ወይም መመሪያ የሚሰርዝ እና የሚተካ ነው።

ቻንስለሩ ያጸደቁት: _____

በስራ ላይ የዋለበት ቀን: ዲሴምበር (December) 28 ቀን 2020

DISTRICT OF COLUMBIA PUBLIC SCHOOLS

በቋንቋ እገዛ የማግኘት (LanguageAccess) ፖሊሲ

I. ዓላማ እና የስፋት-መጠን

ሁሉም ተማሪ የመወደድ ስሜት እንዲሰማው፣ እና በአዎንታዊነት ተጽዕኖ የሚያደርግን ማህበረሰብን ለማዘጋጀት እና ጠንካራና ሁሉን አካታች የሆነ የመማሪያ አካባቢዎችን ለሁሉም ተማሪዎች በመስጠት በሕይወታቸው እንዲበለጽጉ መደረጉን ለማረጋገጥ፤ የኮሎምብያ ዲስትሪክት የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS) በቁርጠኝነት ይሰራል። የቀድሞ መነሻቸው ወይም ሁኔታቸው ምንም ሆነ ምን፣ ዓለም-አቀፍ ደረጃን የጠበቀ ትምህርትን መስጠት፤ የእንግሊዘኛ ቋንቋን እንደ ተቀዳሚ ቋንቋነት የማይጠቀመውን - በቋንቋ እና በባህል ላይ ስብጥር ያለውን፣ የኮሎምቢያ ዲስትሪክት ማህበረሰቦችን ሁሉን ያካተተ ጠንካራ ግንኙነትን የሚገነባ እና የሚጠብቅ የቋንቋ እገዛ የማግኘት እርዳታን መስጠት፤ DCPS-በተልዕኮው በድጋሚ ያረጋግጣል።

ይህ ፖሊሲ የሚያስተላልፈው፤ በDCPS የቋንቋ ማግኛ መስፈርቶች መሠረት፣ ውስን እና ምንም-የእንግሊዘኛ ችሎታ ያላቸው ባለድርሻ አባላት (stakeholders)፣ በDCPS የሚሰጡ መረጃዎችን ማግኘት መቻላቸውን ለማረጋገጥ ነው።[1] የዚህ ፖሊሲ ዓላማ፣ ሰፊው ሕዝብ ማግኘት እንዲችል እና በመንግስታዊ አገልግሎቶች፣ ፕሮግራሞች እና እንቅስቃሴዎች መካፈል እንዲችሉ ለማበረታታት፣ በተስተካከለው፤ የ2004ቱ በቋንቋ እገዛ ማግኛ ድንጋጌ (Language Access Act of 2004)፣ መስፈርትነቱን ለማስተላለፍ ነው።[2] ይህ ፖሊሲ፣ የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞችን፣ የትብብር ፕሮግራም ሠራተኞች፣ የልምምድ ሠራተኞች (interns)፣ አብረው የሚሰሩ (fellows)፣ እርዳታ ሰጪዎች፣ የኮንትራት ሠራተኞች፣ ተዛማጅ-የሆኑ ሠራተኞች፣ እና ሌሎች በቀጥታ ወይም በDCPS አማካኝነት ከሕዝቡ ጋር ግንኙነት የሚያደርጉ ተቋማትን ወይም ግለሰቦችን ጨምሮ፤ ሁሉንም የDCPS ተቀጣሪ-ሠራተኞችን እና ተዛማጅ ግለሰቦችን የሚመለከት ይሆናል።[3]

II. ሥልጣን እና በስራ ላይ የሚውል ሕግ

ምንጭ	ጥቅስ (Citation)
የፌደራል ሕግ	- አንቀጽ 6 (Title VI) የ1964 የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ (Civil Rights Act)፣ በኮድ የተለየበት በ42 U.S.C. § 2000d - ከጉዳተኝነት ጋር የሚገኙ ግለሰቦች ድንጋጌ (Individuals with Disabilities Education Act (IDEA), 20 U.S.C. §§ 1400, et seq - የ1973 ክፍል (Section) 504 መልሶ-ማቋቋም ድንጋጌ (Section 504 of the Rehabilitation Act of 1973 (Section 504), as amended, 29 U.S.C. § 794 - የ1974 በትምህት እኩል ዕድሎችን የማግኘት ድንጋጌ (Equal Educational Opportunities Act of 1974, 20 U.S.C. §§ 1701, et seq.
የፌደራል ደንቦች	- IDEAን የመተግበት ደንቦች፣ 34 C.F.R. §§ 300, et seq.
የኮሎምብያ ዲስትሪክት ሕግ	- በ2004ቱ የዲሲ የቋንቋ እገዛ ማግኘት ድንጋጌ (DC Language Access Act of 2004) codified at D.C. Code §§ 2-1931, et seq. - የዲሲ የሰብዓዊ መብቶች ድንጋጌ (DC Human Rights Act) codified at D.C. Code §§ 2-1401.01, et seq
የኮሎምብያ ዲስትሪክት የማዘጋጃ ቤት ደንቦች	- 4 DCMR §§ 1200, et seq. (የሰብዓዊ መብቶች በቋንቋ እገዛ ማግኛ ድንጋጌ ቢሮ (Office of Human Rights Language Access Act) - 5-E DCMR §§ 2600, et seq. (የተማሪ መዝገቦችን (Student Records) ማግኘት) - 5-E DCMR § 3102 (የቋንቋ ትምህርት ለአናሳ (Minority) ተማሪዎች: ለወላጆች ማስታወቂያ)

[1] This policy does not address DCPS requirements to ensure that English learner (EL) students can participate meaningfully and equally in educational programs. For information about EL support, please visit the DCPS Supports for English Learners website at https://dcps.dc.gov/service/supports-english-learners-els.

[2] *See* D.C. Code §§ 2-1931, et seq.; *see also* D.C. Code § 2-1931(3) (designating DCPS as a covered entity with major public contact).

[3] This policy supersedes past or existing DCPS policy on language access, including the DCPS Interpretation and Translation Policy of 2015.

III. ትርጓሜዎች

ማግኘት ወይም መካፈል ማለት፣ እንዲያውቁት መደረግ፣ እንዲካፈሉ መደረግ እና የእንግሊዘኛ ቋንቋን ከሚያውቁ ግለሰቦች እኩል በሆነ ደረጃ በDCPS የተሰጡ - የሕዝብ አገልግሎቶች፣ ፕሮግራሞች፣ እና እንቅስቃሴዎች ጥቅማ ጥቅሞችን ማግኘት ማለት ነው። (D.C. Code § 2- 1931(1))

ባለሁለት ቋንቋ (Bilingual) ሠራተኛ ማለት፣ በእንግሊዘኛ ቋንቋ እና ከእንግሊዘኛ ሌላ በሆነ ቋንቋ፣ በሁለቱም - ችሎታ እንዳለው በDCPS ተወስኖ የተረጋገጠለት፣ ተቀጣሪ-ሠራተኛ ማለት ነው። (4 DCMR § 1299.1 ይመልከቱ)

የግል የትምህርት ፕሮግራም (Individualized education program (IEP) ማለት፣ ከጉዳተኝነት ጋር ለሚገኙ ግለሰቦች የትምህርት ድንጋጌ (Individuals with Disabilities Education Act) በሚጠይቀው መሠረት፣ ከጉዳተኝነት ጋር የሚገኝን ልጅ፣ ልዩ የሆነውን የትምህርት ፍላጎቶችን ለማሟላት - የልዩ ትምህርት (Special Education) እና ተዛማጅ አገልግሎቶችን የሚገልጽ፤ የጽሁፍ-መግለጫ (written statement) ማለት ነው። (20 U.S.C. § 1401(14) ይመልከቱ)

ማስተርጎም (Interpretation) ማለት፣ በአፍ/የቃል-ንግግር ትርጉም፣ ከአንድ ቋንቋ ወደ ሌላው ቋንቋ፤ ወይም በተቃራኒው፣ የሚደረግ ምልልስ ማለት ነው። ሦስት (3) ዓይነት የማስተርጎም አይነቶች አሉ፤ እነዚህም በአካል ተገኝቶ (in person) ወይም በርቀት በስልክ ወይም በቪዲዮ-ኮንፈረንስ የሚደረግ ነው:

- **ሳይት (Sight) ትርጉም፤** ይህ ዓይነቱ ማስተርጎም፣ አስተርጓሚው የጽሁፍ ሰነድን በአንድ ቋንቋ እያነበበ ወደሚተረጎመው ሌላ ቋንቋ በቃል በመናገር ሲተረጉም ነው፣
- **ተከታታይ (Consecutive) ማስተርጎም፣** በዚህ ዓይነቱ ማስተርጎም፣ ተናጋሪው በቃል-ተናግሮ ሲያቆም፣ ያንን የተናገረውን አስተርጓሚው ሲያስተረጉም ነው፣ እና
- **በተመሳሳይ-ጊዜ (Simultaneous) ማስተርጎም፣** በዚህ ዓይነቱ ማስተርጎም፣ አስተርጓሚው ዋናውን ቋንቋ ከሚናገረው ሰው እኩል የተናገረውን በተመሳሳይ ጊዜ ሲያስተረጉም ነው። (4 DCMR § 1299.1)

የአናሳ ቋንቋ ተማሪ (Language minority student) ማለት፣ ከቤተሰብ መነሻ መሠረቱ (background) የተማረው ከእንግሊዘኛ ቋንቋ ሌላ የሆነን ቋንቋ የሚረዳ እና የሚናገር ተማሪ ወይም ከእንግሊዘኛ ቋንቋ ሌላ የሆነ ቋንቋ በመኖሪያ ቤት ውስጥ የሚነገርበት የቤተሰብ መነሻ መሠረቱ (background) ጋር የሚገኝ ተማሪ ማለት ነው። (5-E DCMR § 3199.1)

ውስን ወይም ምንም-የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታ ((LEP/NEP) ማለት፣ በመናገር ወይም በመፃፍ፤ እንግሊዘኛ-ቋንቋን በቂ በሆነ ሁኔታ መገንዘብ ወይም እራስን ለመግለጽ አለመቻል ማለት ነው። (D.C. Code § 2-1931(5))

ውስን የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታ (LEP) ግለሰብ ማለት፣ በተቀዳሚ ቋንቋነት የእንግሊዘኛ ቋንቋን የማይናገር ግለሰብ፣ እና እንግሊዘኛ ቋንቋን ለማንበብ፣ ለመናገር፣ ለመጻፍ፣ ወይም ለመረዳት፤ ውስን የሆነ ችሎታ ያለው ማለት ነው። (4 DCMR § 1299.1)

ምንም-የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታ (NEP) ግለሰብ ማለት፣ በማንኛውም ትርጉም-ሰጪ በሆነ ደረጃ፣ የእንግሊዘኛ ቋንቋን መናገር ወይም መረዳት የማይችል ግለሰብ ማለት ነው። (4 DCMR § 1299.1)

የቃል (Oral) ቋንቋ አገልግሎቶች ማለት፣ በDCPS የሚሰጡ ፕሮግራሞች ወይም አገልግሎቶችን የLEP/NEP ነዋሪዎች ማግኘት እንዲችሉ ለማስቻል አስፈላጊ የሆነውን የቃል (Oral) መረጃዎችን ማቅረብ ማለት ነው። ይህ አባባል፤ ሁለት ቋንቋ (bilingual) ሠራተኛን በሕዝብ ግንኙነት የስራ-ቦታዎች ላይ መመደብን፣ ልምድና ስልጠና ያላቸውን የማስተርጎም-ስራ የሚሰሩ ሠራተኞችን ማቅረብ፣ ከስልክ የማስተርጎም ፕሮግራሞች ጋር ኮንትራት መግባት፣ ከግል የማስተርጎም አገልግሎት ሰጪዎች ጋር ኮንትራት ማድረግ፣ እና በማህበረሰብ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች አማካኝነት በሕዝብ የገንዘብ እርዳታ እየታገዙ ለእንደነዚህ ያሉ አገልግሎቶች ተሳታፊ የሆኑ አስተርጓሚዎችን መጠቀምን፤ አባባሉ ያከትታል። (D.C. Code § 2-1931(6))

የሕዝብ ግንኙነት የስራ-ድርሻ ቦታ ማለት፣ ቀደምት የሆነው የስራ-ኃላፊነቶች፤ - በሰላምታ መቀበል፣ ማግኘት፣ ማገልገል፣ ወይም ለሕዝቡ መረጃዎችን ወይም አገልግሎቶችን በመስጠት የሚያገለግል ቅጥር የስራ ድርሻ ቦታ ነው። የሕዝብ ግንኙነት የስራ-ድርሻ ቦታ፣ ከሕዝቡ ጋር የግል ግንኙነቶችን ማድረግ የሚያስፈልገው የስራ ድርሻ ቦታ ነው። (4 DCMR § 1299.1)

ትርጉም (Translation) ማለት፣ የጽሁፍ ግንኙነቶችን፣ ከዋናው የቋንቋ ምንጭ ወደ ሌላኛው የተፃፈ ጽሁፍ ቋንቋ፣ የዋናው ምንጭ ጽሁፍ ትርጉም እና ለማለት የተፈለገው ሳይለወጥ፣ ባህላዊ ይዘቱን በጠበቀ መልኩ በጽሁፍ ማቅረብ ማለት ነው። (4 DCMR § 1299.1)

አስፈላጊ የሆኑ (Vital) ሰነዶች ማለት፤ ማመልከቻዎች፣ ማስታወቂያዎች፣ የአቤቱታ ቅጾች፣ ሕጋዊ ኮንትራቶች፣ እና ተጨባጭ በሆነ (ማለትም በወረቀት ወይም በኤሌክትሮኒክ) አቀማመጥ በDCPS የታተሙ ሁሉን ማዳረሻ (outreach) ቁሳቁሶች - ግለሰቦችን ስለ መብቶቻቸው ወይም የብቁነት መስፈርቶቻቸው ጥቅማ ጥቅሞችን ስለማግኘት እና ስለመሳተፍ የሚያሳውቅ ማለት ነው።

ይህ አባባል፤ ስለ ሕዝብ ትምህርት ቤት የመጠጥ-ውሃ የሙከራ ውጤቶች፣ እና የማስተካከያ እርጃዎችን ማጠናቀቅ በተመለከተ፣ ለወላጆች እና አሳዳጊዎች የተላከ የጽሁፍ መረጃ እና ማስታወቂያን ያካትታል። (D.C. Code § 2-1931(7))

IV. መስፈርቶች

A. አጠቃላይ (General)

በመጡበት ሃገር (national origin) ላይ መሠረት ያደረገ አድልዎ፤ በሁለቱም በፌደራል እና በአካባቢ ሕግ አሠራር፣ ክልክል ነው።[4] ለረጅም-ጊዜ የቆየ የጉዳይ ሕግ እና የፌደራል መመሪያ፣ በቀረጸው መሠረት፣ በመጡበት ሃገር (national origin) የሚደረግ አድልዎ የሚያካትተው፤ ቋንቋው ላይ መሠረት ያደረገ አድልዎ፣[5] እና ሁሉንም የፌደራል የገንዘብ እርዳታ የሚያገኙ፣ DCPSን ጨምሮ፤ ውስን የሆነ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ችሎታ (limited English proficient (LEP) ግለሰቦች፣ ፕሮግራሞቻቸውን እና እንቅስቃሴዎችን ትርጉም-ሰጪ በሆነ መልኩ - ማግኘት እንደቻሉ ለማረጋገጥ፣ የሚያስፈልገውን ተገቢ እርምጃዎች መውሰድ ያስፈልጋቸዋል።

የዲሲ ሕግ፤ ውስን ወይም ምንም-የእንግሊዘኛ ችሎታ (LEP/NEP) ለሆኑ ግለሰቦች፣ ተጨማሪ መብቶችን እና ከለላዎችን ይሰጣል። የዲሲ በቋንቋ እገዛ ማግኛ ድንጋጌ (DC Language Access Act)፤ የዲሲ ኤጀንሲዎችን፣ DCPSን ጨምሮ፤ አስፈላጊ የሆኑ (vital) ሰነዶችን እና የቃል (Oral) ቋንቋ አገልግሎቶችን፣ በDCPS አገልግሎቶች ውስጥ፣ ፕሮግራሞች፣ እና እንቅስቃሴዎችን ለማግኘት ወይም ለመካፈል ለጠየቁ ለLEP/NEP ግለሰቦች፣ የጽሁፍ ትርጉሞችን መስጠት አለበት።[6] የአካባቢው የትምህርት ደንቦች፤ በተጨማሪም በሚጠይቁት መሠረት፣ ለሁሉም የእንግሊዘኛ-ቋንቋን ተናጋሪ ለሆኑ ወላጆች እና አሳዳጊዎች የተሰጠ ሁሉንም መረጃዎችን፤ በመኖሪያ ቤት መነጋገሪያ ቋንቋቸው ለሚጠቀሙ አናሳ-ቋንቋ ተናጋሪ ተማሪዎች ወላጆች እና አሳዳጊዎችም፣ DCPS በማንኛውም ተገቢ ሆኖ በተገኘ ጊዜ፣ መስጠት ያስፈልገዋል።[7]

B. ተለጣፊ ምልክቶች

ሁሉም ትምህርት ቤቶች እና የማዕከላዊ ቢሮ ቦታዎች፤ እንዲሁም የሳተላይት (satellite) ቦታዎች፣ እና በDCPS የኮንትራት ሠራተኞች እና ድጋፍ-ሰጪዎች - DCPSን ወክለው ሕዝቡን በሚያገለግሉበት ጊዜ የሚጠቀሙባቸው ቦታዎች፤ በቋንቋ እገዛን ለማግኘት ያላቸውን መብቶቻቸውን - ለሕዝቡ የሚገልጽ፣ በደንብ የሚታይ ምልክቶችን መለጠፍ አለባቸው። የቋንቋ መለያ ምልክቶች ወይም ፖስተሮች - የማስተርጎም አገልግሎት ማመላከቻ ቻርቶች (interpretation service point charts) ተብሎ በሌላ ስም የሚታወቀው፤ የLEP/NEPው ደንበኛውን ሊያመላክት የሚችልባቸውን የተለመዱ ቋንቋ ዝርዝር የያዘ ሆኖ አገልግሎት ሊጠይቅባቸው የሚችል ሲሆን፣ እና በዲሲ የሰብዓዊ መብቶች ቢሮ እና በDCPS በቋንቋ እገዛ ማግኛ ክፍል (Language Acquisition Division) ውስጥ ይገኛሉ።[8]

C. የጽሁፍ ትርጉም

የዲሲ በቋንቋ እገዛ ማግኛ ድንጋጌ (DC Language Access Act)፣ አስፈላጊ የሆኑ (Vital) ሰነዶችን፣ 3% ወይም 500 ግለሰቦችን ወደ-ያዘው፣ የትኛውም አነስተኛ የሆነን የህብረተሰብ ክፍልን የሚያገለግል ወይም ግንኙነት ሊደረግበት ወደቻለው፤ ወይም ሊገለገልበት ይችላል ወይም ግንኙነት ሊደረግበት ይችላል ወደሚባለው፣ ወደ ማንኛውም እንግሊዘኛ ወዳልሆነ ቋንቋ፣ በLEP/NEP ማህበረሰቡ የመነጋገሪያ ቋንቋ የጽሁፍ ትርጉሞችን፣ DCPS ማቅረብ አለበት።[9] አስፈላጊ የሆነ (Vital)

---

[4] Title VI of the Civil Rights Act of 1964 prohibits recipients of federal financial assistance from discriminating based on race, color, or national origin. *See* Pub. L. 88–352, title VI, §601, July 2, 1964, 78 Stat. 252, codified at 42 U.S.C. § 2000d. The DC Human Rights Act prohibits discrimination by an educational institution based on the actual or perceived national origin of any individual. *See* DC Code § 2-1402.41.

[5] *See Lau v. Nichols*, 414 U.S. 563 (1974); *see also* Department of Justice Guidance to Federal Financial Assistance Recipients Regarding Title VI Prohibition Against National Origin Discrimination Affecting Limited English Proficient Persons, 67 Fed. Reg. 41, 455 (June 18, 2002), *available at* https://www.lep.gov/13166/eo13166.html.

[6] D.C. Code §§ 2-1931, et seq.

[7] 5-E DCMR § 3102.1.

[8] *See* DC Office of Human Rights Language Access Toolkit, *available at* https://ohr.dc.gov/page/LAportal/toolkit; *see also* Language Acquisition Division (LAD) Canvas page, *available at* https://dcps.instructure.com/courses/146048.

[9] *See* D.C. Code § 2-1933(a); 4 DCMR § 1205.2.

ሰነዶች ተብለው በአጠቃላይ የተተረጎሙት፣ ማመልከቻዎች፣ ማስታወቂያዎች፣ የአቤቱታ ቅጾች፣ ሕጋዊ ኮንትራቶች፣ እና ለሁሉም-ማዳረሻ (outreach) በመሆን በወረቀት ላይ የታተሙ ቁሳቁሶች ወይም የኤሌክትሮኒክ ይዘት ያላቸው ስለ መብቶች እና ብቁነት መስፈርቶች - ጥቅማ ጥቅሞችን ለማግኘት እና ለመካፈል፣ ትርጓሜያቸውን ለመግለጽ ለድርጅቶቹ የተተዉ የተወሰኑ ቁሳቁሶች ናቸው።[10]

1. በኤጀንሲ-ደረጃ አስፈላጊ የሆኑ (Vital) ሰነዶች

ከአስፐን (Aspen) የተገኘ፣ የወላጆች/አሳዳጊዎች ተመራጭ የመገናኛ ቋንቋ የመረጃ-ስብስብ (data)ን ጨምሮ፣[11] የተለያዩ የመረጃ-ስብስብ (data) ምንጮች-ምልከታ ላይ መሠረት በማድረግ፣ ስፓኒሽ ቋንቋ፣ በአሁኑ-ጊዜ የትርጉም የደረጃ ገደብ (threshold)፣ በኤጀንሲ-ደረጃ[12] እንደሚያሟላ፣ እና በኤጀንሲ-ደረጃ አስፈላጊ የሆኑ (Vital) ሰነዶች ማለትም፤ አስፈላጊ የሆኑ (Vital) ሰነዶች ማለት፣ ለሁሉም ትምህርት ቤቶች እና የዲሲ ማህበረሰብ የሚያስፈልግ) በመሆኑ በወቅቱ ወደ ስፓኒሽ እንዲተረጎም፣ DCPS ወስኗል። አቅም እንደፈቀደ፣ በኤጀንሲ-ደረጃ አስፈላጊ የሆኑ (Vital) ሰነዶች ወደ ሌሎቹ በየትምህርት ቤቱ፣ የደረጃ ገደብ (threshold) በሚያሟሉ ቋንቋዎች (ማለትም፤ በአሁኑ-ወቅት አማርኛ እና ቻይኒኛ) ቋንቋዎች ይተረጎማሉ።

እነዚህ የሚከተሉትን ጨምሮ፣ ነገር ግን በዚህ ብቻ ሳይወሰን፤ በኤጀንሲ-ደረጃ አስፈላጊ የሆኑ (Vital) ሰነዶች፣ በትምህርት ቤቶች ውስጥ ጥቅም ላይ እንዲውሉ፣ የDCPS ማዕከላዊ ቢሮ መተርጎማቸውን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለበት:

- የመመዝገቢያ እና የምዝገባ መረጃዎች እና ቅጾች፣
- የሂደት ሪፖርቶች እና የሪፖርት ካርድ ቅጾችን፣
- የተማሪ የስነምግባር ማገጃ (suspension)/መባረር (expulsion) ማስታወቂያዎች እና አቤቱታ የማቅረብ መብቶች፤ እና
- በእንግሊዘኛ ቋንቋ መማር አገልግሎቶች ውስጥ ያሉ ተማሪዎች ወላጆች የሚላክ ማስታወቂያዎች።

2. በትምህርት ቤት-ደረጃ አስፈላጊ የሆኑ (Vital) ሰነዶች

በትምህርት ቤት-ደረጃ አስፈላጊ የሆኑ (Vital) ሰነዶች (ማለትም፤ በትምህርት ቤቱ የተዘጋጁ አስፈላጊ የሆኑ (Vital) ሰነዶች)፣ በኤጀንሲ-ደረጃ ገደብ የቋንቋ ምድብ (threshold languages) ውስጥ ባለ (ማለትም፤ ስፓኒሽ)፤ ቢያንስ አንዱ ወላጅ ስፓኒሽ ተመራጭ ቋንቋው እንደሆነ ካሳወቀ እና በሌሎች በቀሪዎቹ ቋንቋዎች፣ የ3%/500 ግለሰቦችን፣ በግለሰቡ ትምህርት ቤት ውስጥ "ግንኙነት ያደረጉ ወይም ግንኙነት ሊያደርጉ ይችላሉ ተብሎ በሚጠበቅ" የደረጃ ገደብ (threshold) የሚያሟሉ ናቸው። በአሁኑ ጊዜ፤ በአማርኛ፣ በቻይኒኛ፣ እና በስፓኒሽ (ሽፋን-ያገኙ ቋንቋዎች) በበርካታ ትምህርት ቤቶች ውስጥ የደረጃ ገደብ (threshold)ን የሚያማሉ ቋንቋዎች ናቸው።[13]

የትምህርት ቤት ሠራተኞች፣ ከሕዝብ ግንኙነት ጋር የሚገኙ የኮንትራት ሠራተኞች/ድጋፍ ሰጪዎች፣ እና የሕዝብ ግንኙነት የማዕከላዊ ቢሮ ፕሮግራሞች፤ በትምህርት ቤት ደረጃ፣ በሚያስፈልገው ቋንቋ(ዎች) የጽሁፍ ትርጉሞችን መቅረባቸው የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው።

3. ሰነዶቹ፤ በLEP/NEP የግለሰቡ ቋንቋ አልተገኙም

ሰነዶቹ፤ በLEP/NEP የግለሰቡ ቋንቋ፣ መገኘት ካልቻለ፣ (ለምሳሌ፤ የደረጃ ገደብ የቋንቋ ምድብ (threshold languages) ውስጥ ካለው ቋንቋ ውጪ በሆነ ቋንቋ ግለሰቡ የሚናገር ከሆነ፣ ወይም አስፈላጊ (vital) የሆነ ሰነድ ነው ተብሎ ካልተወሰደ)፣ ከትምህርት ቤቱ የሁለት-ቋንቋ ተናጋሪ ሠራተኛ እገዛ እየተደረገ፣ የጽሁፍ መረጃው በስልክ በቃል ግንኙነት ሊነገራቸው የሚችል ሲሆን፣ የሚገኝ ከሆነ ደግሞ በስልክ አማካኝነት በቋንቋ-መስመር (Language Line) የስልክ ትርጉምን በመጠቀም ይሰጣል።

[10] D.C. Code § 2-1931(7). With respect to education documents, vital documents include lead water testing results for DCPS public schools provided to the Chief Operating Officer by the Department of General Services that show a lead concentration over 5 parts per billion. *See* DC Code § 38-825.01a(a)(2).

[11] Information about a parent's/guardian's preferred language for correspondence can be found in the student's Aspen record under the "Student" tab. *See* LAD Canvas page, *available at* https://dcps.instructure.com/courses/146048, for more information on how to obtain families' language preferences from Aspen.

[12] Data sources include the number of English learners served by DCPS, the number of families expressing a preference to receive communications in a non-English language, and DC census and demographic data.

[13] *See* LAD Canvas page, *available at* https://dcps.instructure.com/courses/146048, for the list of languages that meet the threshold in each school.

D. የቃል (Oral) ቋንቋ አገልግሎቶች

ሁሉ የDCPS ትምህርት ቤቶች፣ የሕዝብ ግንኙነት ማዕከላዊ ቢሮ አባላቶች፣ እና የሕዝብ ግንኙነት የኮንትራት ሠራተኞች ወይም ድጋፍ-ሰጪዎች፤ በDCPS አገልግሎቶች ውስጥ፣ ፕሮግራሞች፣ እና እንቅስቃሴዎችን ለማግኘት ወይም ለመካፈል ለጠየቁ የLEP/NEP ግለሰቦች፣ የቃል (Oral) ቋንቋ አገልግሎቶችን መስጠት ያስፈልጋቸዋል።[14] ይህ የሚያካትተው፤ ስለእንግሊዘኛ-ቋንቋ ተማሪው አገልግሎቶች ያለውን መረጃ ወይም በሚገነዘቡት ቋንቋ ብቁነት መሰጠቱን ለማረጋገጥ፤ ለእንግሊዘኛ ቋንቋ ተማሪዎች ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ የቃል (Oral) ቋንቋ አገልግሎቶች ይሰጣል። በጽሁፍ ከሚሰጡ ትርጉሞች ጋር ባልተመሳሰለ ሁኔታ፤ የቃል (Oral) ቋንቋ አገልግሎቶችን ለመስጠት የሚያስፈልገው መስፈርት፣ ከላይ የተጠቀሰውን በሚሸፈኑ-ቋንቋዎች ብቻ የተወሰነ አይደለም።

በDCPS ትምህርት ቤቶች እና የሕዝብ ግንኙነት ማዕከል ቢሮ አባላቶች እንደሚሰጡት ዓይነት የሆኑት የቃል (Oral) ቋንቋ አገልግሎቶች፣ በሚከተለው መሠረት የሚወሰኑ ይሆናል:

- አገልግሎት ያገኙ ወይም ግንኙነት ሲያደርጉ የነበሩ፣ የLEP/NEP ግለሰቦች፤ ወይም አገልግሎት ወይም ግንኙነት ሊያገኙ ይችሉ ይሆናል ተብሎ የሚገመተው፤ ቁጥር ወይም ተመጣጣኝነት - በትምህርት ቤት ወይም በቡድን ሲታይ፤
- የLEP/NEP ግለሰቦች ከትምህርት ቤቱ ጋር ወይም ከቡድኑ ጋር ለማነጋገር የመጡበት ድግግሞሾች፣
- በትምህርት ቤቱ ወይም ቡድኑ የተሰጠው አገልግሎት ያስገኘው ጥቅም፣ እና
- ሊገኙ የሚችሉ የመረጃ ምንጮች (resources)።[15]

የDCPS ትምህርት ቤቶች፣ የቃል (Oral) ቋንቋ አገልግሎቶችን በስልክ፣ በአካል ተገኝቶ (in person)፣ ወይም በቪዲዮ ኮንፈረንስ፤ ቀደምት በሆነው ቋንቋቸው LEP/NEP ውስጥ ለተመደቡ ወይም የመጀመሪያ የመግባቢያ ቋንቋቸው እንግሊዘኛ ላልሆነ ሁሉ፤ መስጠት አለበት። የቃል (Oral) ቋንቋ አገልግሎቶች የሚከተሉትን ማካተት እና በሚከተለው መንገድ መስጠት አለበት:

- በሕዝብ ግንኙነት የስራ-ቦታዎች ላይ፣ በማንኛውም በተገቢው ሁኔታ አስፈላጊ በሚሆን ጊዜ፤ ሁለት ቋንቋ (bilingual) ሠራተኛን መመደብ፣
- ልምድ ያላቸው እና ስልጠና ያላቸውን የማስተርጎም ስራ የሚሰሩ ሠራተኞችን ማቅረብ፣
- የስልክ የማስተርጎም አገልግሎት ፕሮግራሞች ጋር ኮንትራት ማድረግ፣ እና
- ከግል የማስተርጎም አገልግሎት ሰጪዎች ጋር ኮንትራት ማድረግ፣ ወይም በማህበረሰብ አገልግሎት ሰጪ ድርጅቶች አማካኝነት በሕዝብ የገንዘብ እርዳታ እየታገዙ ለእንደነዚህ ያሉ አገልግሎቶች ተሳታፊ የሆኑ አስተርጓሚዎችን መጠቀም።[16]

የሚሰጠው መረጃ ወይም እንዲደርስ የተፈለገው ግንኙነት፣ ጥቅማጥቅሞችን ስለማግኘት ወይም ትምህርታዊ ውሳኔዎች ለማድረግ፣ እንደ ልዩ የትምህርት ስብሰባዎችን መካፈል ያሉትን የሚያካትት ከሆነ፤ ልምድና ስልጠና ያለው የሁለት ቋን ቋ ተናጋሪ የሆነ የማስተርጎም ሠራተኛው፣ ወይም ባለሞያ አስተርጓሚው አገልግሎት እንዲሰጥ መደረግ አለበት። ማንኛውም የሚያስተረጉም፣ የሁለት ቋንቋ (bilingual) ተቀጣሪ ሠራተኛ፤ ገለልተኛ መሆን እና በጎንዮሽ-ሌላ የጥቅም ቅራኔ (conflict of interest) ሊፈጥር የሚችሉ ነገሮች በሙሉ ማሳወቅ አለበት። የስልክ የማስተርጎም አገልግሎት ለመስጠት፣ አስተርጓሚ ያልተገኘለት - በጣም ብዙ ጊዜ የማይገጥም አናሳ (minority) ቋንቋዎች የገጠመው የDCPS ሠራተኛ፤ በማስተማርና መማር (Teaching and Learning) ቢሮ ውስጥ በሚገኘው በቋንቋ እገዛ ማግኛ ክፍል (Language Acquisition Division) ውስጥ ያሉትን ዋና አስተዳዳሪ ማነጋገር አለበት።

የLEP/NEP ግለሰቡ፣ DCPS ያቀረበው አስተርጓሚ - በቂ የሆነ፣ ትክክለኛ፣ ወይም የማያዳላ ትርጉምን በስብሰባው ላይ መስጠቱ ላይ ካልተማመነበት፤ በስብሰባው ላይ አስተርጓሚው ማስተርጎሙን እንዳይቀጥል፣ የLEP/NEP ግለሰቡ መጠየቅ ይችላል። ከዚህ በኋላ፣ የDCPS ሠራተኛው፣ ሌላ አስተርጓሚ ማዘጋጀት አለበት። በአስተርጓሚው የሙያ-ብቃት ወይም አለማዳላትን በተመለከተ፣ የLEP/NEP ግለሰቡ ያሉት ስጋቶች በትምህርት ቤት ደረጃ መፈታት ካልቻሉ፣[17] ግለሰቡ፤ በቋንቋ እገዛ ማግኛ ክፍል (Language Acquisition Division) ውስጥ፣ የቋንቋ ማግኛ ዩኒት (Language Access Unit)ን እንዲያነጋግሩ ይመከራሉ።

[14] *See* DC Code § 2-1932(a).
[15] D.C. Code § 2-1932(b).
[16] D.C. Code § 2-1931(6).
[17] School staff can attempt to resolve such concerns by, for example, ending the call and calling the Language Line back for a different interpreter or ending the meeting early and arranging for a different interpreter.

ከተማሪው የጤና እና የደህንነት ሁኔታ ጋር የተያያዘ የአስቸኳ-ጊዜ የአደጋ ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር ወይም የLEP/NEP ግለሰቡ እንዳይደረግ አበክሮ-በጠየቀበት ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር፣[18] የDCPS ሠራተኛው፤ ለLEP/NEP ግለሰቡ፣ በተማሪዎች ወይም በሌላ የቤተሰብ አባላቶች በሚሰጥ የቃል ትርጉም አገልግሎቶች ላይ ተማምኖ መጠቀምን ይከለክላል፡፡

E. ከጉዳተኝነት (Disabilities) ጋር የሚገኙ ተማሪዎች

1. ከጉዳተኝነት ጋር የሚገኙ ግለሰቦች የትምህርት አሰጣጥ ድንጋጌ (Individuals with Disabilities Education Act) ስር

ከጉዳተኝነት ጋር የሚገኙ ግለሰቦች የትምህርት ድንጋጌ (Individuals with Disabilities Education Act (IDEA) ስር፣ ከጉዳተኝነት ጋር የሚገኘው ልጅ ወላጅ፣ በእያንዳንዱ የግል የትምህርት ፕሮግራም (Individuals with Disabilities Education Act (IDEA) የቡድን ስብሰባ ውስጥ እንዲካፈሉ ወይም የመካፈል ዕድል መሰጠቱን DCPS ለማረጋገጥ እርምጃዎችን መውሰድ አለበት።[19] ትምህርት ቤቱ በተጨማሪም፣ በIEP ስብሰባ ወቅት፣ "ወላጅ ሂደቶቹን መረዳቱን ለማረጋገጥ ማንኛውንም የሚያስፈልጉ እርምጃዎች መወሰዱን ለማረጋገጥ"፤ አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝ ጊዜ የአስተርጓሚ አገልግሎቶችን ማዘጋጀትን ጨምሮ፤ ማድረግ አለበት።[20] ይህ ወላጆች በልዩ ትምህርት አገልግሎት ውስጥ ስምምነታቸውን ለመስጠት "ስምምነት ስለሚሰጡበት ተዛማች እንቅስቃሴዎች ውስጥ በሁሉም መረጃዎች ላይ፣ በአፍ-መፍቻ ቋንቋው/ቋንቋዋ፣ ወይም በሌላ የመገናኛ መንገድ ተጠቅመው" ተረድተው ካወቁ በኋላ ብቻ ስምምነት መስጠታቸውን ለማረጋገጥ ነው።[21]

የIDEA፣ የ'Title VI' of the Civil Rights Act of 1964፣ የ'Equal Educational Opportunities Act of 1974'፤ እና ከእነዚህ ጋር የሚሄዱ ድንጋጌዎች፤ የልዩ ትምህርት ሰነዶችን ለወላጆች/አሳዳጊዎች የመተርጎምን አስፈላጊነት በበርካታ ድንጋጌዎቻቸው ውስጥ አካተዋል። በፌደራል እና በአካባቢው መስፈርቶች ስር እንዳው ሁሉ፤ DCPS፣ የሚከተሉትን በሙሉ - ለወላጅ/አሳዳጊ ለማስተርጎም እና ለመስጠት ዝግጁ መሆን አለበት:

- IEPዎች እና የIEP ማስተካከያዎች፣
- በግምገማ፣ ብቁነት መወሰኛ፣ የIEP እድገት/መዳበር፣ የIEP አፈፃፀም፣ እና የIEPው ቁጥጥር ቀስ-በቀስ የሚደረግ የIEP ሂደት ውስጥ፣ ሁሉም ከIEP ጋር ተዛማች የሆኑ ጠቃሚ የሆኑ ሰነዶች፣ ለወላጆች/አሳዳጊዎች መሰጠት አለበት። ይህን መስፈርት ለማሟላት፤ የDCPS ሠራተኛው፣ በስቴት የትምህርት የበላይ ተቆጣጣሪ ቢሮ (Office of the State Superintendent of Education (OSSE) የተሰጠውን በቋንቋ ቅጾችን ተጠቅሞ እና የተተረጎመውን ተማሪውን የተመለከተ መረጃ ያስገባል። የDCPS ሠራተኞች፣ በIEP ሂደቱ ወቅት ለወላጆች/አሳዳጊዎች ማስተርጎም የሚያስፈልጓቸው ሰነዶች ምሳሌዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ:
    - የግብዣ ደብዳቤዎች እና የስብሰባ ማስታወቂያዎች፣
    - በወላጆች/አሳዳጊዎች ምልከታ ሊደረግባቸው እና መፈረም የሚያስፈልጋቸውን የስምምነት መስጫ ቅጾች፣
    - ወደ IEP ግቦች ያለውን የተማሪ ሂደት የሚከታተል የሂደት ሪፖርቶች፣ እና
    - የተራዘመ የትምህርት ዓመት (Extended School Year (ESY) የብቁነት ሰነድ

የወላጅ/አሳዳጊ ተመራጭ የሆነው የመግባቢያ ቋንቋ በድርጅቱ-የደረጃ ገደብ የቋንቋ ምድብ ውስጥ የሚገኝ ከሆነ (ማለትም፤ ስፓኒሽ)፣ የተተረጎመው IEP እና የተስተካከለው IEP፣ የእንግሊዘኛ ስሪት የሆነው IEP እና የተስተካከለውን IEP ለወላጅ/አሳዳጊ ከተሰጠበት በ45 ቀናት ውስጥ፣ ወላጅ/አሳዳጊ የተተረጎመውን ሰነዶች የማግኘት መብቶቻቸውን ካላነሱ (waive እስካላደረጉ) ድረስ[22]፤ ለወላጅ/አሳዳጊ ሊሠጣቸው ይገባል። ለሌላ ከIEP ጋር የተዛመዱ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች፣ በድርጅቱ-የደረጃ ገደብ የቋንቋ ምድብ (threshold language) በሚተረጎምበት ቋንቋ፣ (ማለትም፣ ስፓኒሽ) ጊዜውን በጠበቀ ሁኔታ መሠጠት አለበት።

[18] *See* LAD Canvas page, *available at* https://dcps.instructure.com/courses/146048, for the interpretation waiver form to document that an LEP/NEP individual has waived this right.
[19] *See* 34 CFR § 300.501(b).
[20] *See* 34 CFR § 300.322(e).
[21] *See* 34 CFR § 300.9.
[22] *See* LAD Canvas page, *available at* https://dcps.instructure.com/courses/146048, to obtain the waiver form.

የወላጅ/አሳዳጊ ተመራጭ የሆነው የመግባቢያ ቋንቋ በድርጅቱ-የደረጃ ገደብ የቋንቋ ምድብ (threshold language) ውስጥ ካልሆነ (ለምሳሌ፣ ከስፓኒሽ ሌላ የሆነ ቋንቋ)፤ በወላጅ/አሳዳጊ በተጠየቀ ጊዜ፣ ጊዜውን-በጠበቀ ሁኔታ IEPው ተተርጉሞ ለወላጅ/አሳዳጊ መሰጠት አለበት። ለሌሎች ከIEP-ጋር ተዛማጅ የሆኑ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶች፣ ተገቢ-ሆኖ እስከተገኘ ድረስ፤ ትርጉሞች መቅረብ አለባቸው። ሌሎች ከIEP-ጋር ተዛማጅ የሆኑ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን DCPS ለማስተርጎም ካልቻለ፣ ተተርጉሞ በተሰጠው ማጠቃለያ (summary) አማካኝነት፣ በጽሁፍ፤ ወይም ከትምህርት ቤቱ የሁለት ቋንቋ ተናጋሪ ሠራተኛ (የሚገኝ ከሆነ) ወይም የቋንቋ እርዳታ መስመርን (Language Line) በመጠቀም፣ በቃል ሊነገራቸው ያስፈልጋል።

ከOSSE-የተዘጋጀ ለትርጉም በቅድሚያ-የተቀረጹ (templates) በማይኖሩ ጊዜ፣ ሌሎች ከIEP-ጋር ተዛማጅ የሆኑ አስፈላጊ የሆኑ ሰነዶችን፤ DCPS ቢያንስ፣ አግባብ ያለውን ማጠቃለያውን (summary) መረጃ፣ ለወላጅ/አሳዳጊ የሰነዱን ቁልፍ ይዘቶችን ለማሳወቅ በቂ የሚሆነውን ያህል፣ ማስተርጎም አለበት። ለምሳሌ፤ ሙሉ የሆነውን የግምገማ ሪፖርት እንደ ተማሪው የግምገማ ሂደት ሆኖ (ለምሳሌ፤ የስነ-ልቦናዊ፣ የንግግር ግምገማ) የተካሄደውን - ከመተርጎም ይልቅ፤ የLEP/NEP ወላጅ መረዳት የሚገባውን የግምገማውን ውጤቶች የሚያሳየውን፣ ግኝቱን እና የሚመከረውን ሃሳቦች ማጠቃለያ (summary)ን፣ DCPS የሚያስተረጉም ይሆናል።

ስለ ወላጅ/አሳዳጊ ለመነጋገሪያ ተመራጭ የሆነ ቋንቋ የሚናገር መረጃን፣ በተማሪው የአስፐን (Aspen) መዝገብ ስር፣ በ“Student” ማውጫ (tab) ስር፣ ስር የሚገኝ ይሆናል።[23]

2. በ1973 የክፍል (Section) 504 መልሶ-የማቋቋም ድንጋጌ (Rehabilitation Act)

የ1973 የክፍል (Section) 504 መልሶ-የማቋቋም ድንጋጌ፣ በተስተካከለው መሠረት፤ በሁሉም የፌደራል የገንዘብ እርዳታን የሚያገኙ ፕሮግራሞች ውስጥ፣ ከጉዳኝነት ጋር በሚገኙ ግለሰቦች ላይ አድልዎን የሚከለክል ነው። በሕዝብ ትምህርት ቤቶች ውስጥ፣ ክፍል (Section) 504፤ ብቁ ለሆኑ ከጉዳተኝነት ጋር ለሚገኙ ተማሪዎች፣ አጠቃላይ የትምህርት አሰጣጥ ስርዓተ ትምህርትን፣ የመማር ዕድልን፣ እና የትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎችን፤ ልክ እንደ ከጉዳተኝነት-ጋር የማይገኙ እኩዮቻቸው[24]አንድ-ዓይነት በመሆነ መንገድ፣ ማመቻቻዎችን እና ተያያዥ-የሆኑ አገልግሎቶችን ያቀርባል። የDCPS 504 ቡድኖች፣ ወላጆችን/አሳዳጊዎችን በ504 ሂደት ላይ መጠነ-ሰፊ በሆነ መንገድ እንዲሳተፉ ሙከራ በማድረግ እና ለLEP/NEP ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ የአስተርጓሚ አገልግሎቶችን በሚያስፈልግ ጊዜ በማዘጋጀት ሁልጊዜ እንዲካፈሉ ማድረግ አለባቸው። ሽፋን-ካገኙት ቋንቋዎች ውስጥ ያለውን አንዱን ቋንቋ የሚናገሩ ወላጆች/አሳዳጊዎች፤ ጊዜውን በጠበቀ ሁኔታ ወላጁ/አሳዳጊው በመረጠውን ቋንቋ የተማሪው 504 ዕቅድ መተርጎም አለበት። ሽፋን ከተሰጣቸው ቋንቋዎች ውስጥ ያሉ ቋንቋዎችን የማይናገሩ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ የ504 ዕቅድ የትርጉም አገልግሎቱ፣ አቅም-በፈቀደ መጠን ጥያቄው ሲቀርብ የሚሰጥ ይሆናል።

F. የመረጃ- ስብስብን (Data)፣ መሠብሰብ

የዲሲ በቋንቋ እገዛ ማግኛ ድንጋጌ (DC Language Access Act)፤ ስለሚነገሩ ቋንቋዎች እና በዚያ በተወሰነ ቋንቋ የLEP/NEP ደንበኞች ቁጥር ላይ የመረጃ-ስብስብ (data)ን፣ DCPS እንዲሰበስብ ይጠይቃል። ወላጆች/አሳዳጊዎች የሚመርጡትን የመግባቢያ-ቋንቋቸውን ካሳዩበት ከምዝገባ ቅጽ ላይ፣ ይህን መረጃ በቀደምትነት DCPS የሚሰበስብ ይሆናል። ከዚያ በኋላ፣ ይህ መረጃ በተማሪው የአስፐን (Aspen) መዝገብ፣ በ“Student” ማውጫ (tab) ስር የሚመዘገብ ይሆናል።

የዲሲ በቋንቋ እገዛ ማግኛ ድንጋጌ፣ በDCPS ሠራተኞች/የኮንትራት ሠራተኞች እና በLEP/NEP ግለሰቦች መካከል ስለተፈጠሩ ገጠመኞችም የመረጃ-ስብስብ (data)ን፣ እንዲሰበስቡም ይጠይቃቸዋል። ይህ መረጃ፤ በኮንትራክተሮች፣ በቋንቋ እገዛ መስጫ ተወካዮች፣ እና ሌሎች ሠራተኞች መሰብሰብ ያለበት እና ጊዜውን በጠበቀ ሁኔታ ወደ በቋንቋ እገዛ ማግኛ ክፍል መሰጠት አለበት። የቋንቋ እገዛ ማግኛ ክፍል፤ ይህን የመረጃ-ስብስብ (data)ን እንዴት ማስገባት እንደሚቻል፣ ለሠራተኞች/ኮንትራክተሮች በቀጥታ ያሳውቃቸዋል። ወደ የሰብዓዊ መብቶች ቢሮ (Office of Human Rights (OHR)፣ መረጃው ተልኳል።

[23] *See* LAD Canvas page, *available at* https://dcps.instructure.com/courses/146048, for more information on how to obtain families' language preferences from Aspen.
[24] *See* 29 U.S.C. § 794; 34 CFR § 104.36.

G. ሥልጠና

ሁሉም የDCPS ተቀጣሪ ሠራተኛ እና በሕዝብ ግንኙነት የስልጣን ቦታዎች ላይ የሚገኙ ተዛማጅ የሆኑ ግለሰቦች፤ የLEP/NEP ግለሰቦችን እና በቋንቋ እና በባህል ስብጥር ያላቸውን ህዝቦች ለማገልገል፣ መስፈርቶቹን እና ሕጋዊ ግዴታዎችን ብቃት ያለው-ደረጃ ሊኖራቸው ይገባል። በዚህም መሠረት፤ አባላቶቹ፣ ወይ ድህረ-ገጽን መሠረት ያደረገ (web-based) ወይም በአካል ተገኝቶ (in-person) በDCPS የሚሰጡ ስልጠናዎችን፣ ማስታወቂያው በሚወጣ ጊዜ መውሰድ አለባቸው። ለአዲስ ሠራተኞች፣ እንደ-አዲስ መጪዎች ሂደት አንዱ አካል በመሆን እና ለቀድሞ-ሠራተኞች ደግሞ እንደ ቀጣይነት እንዳለው የሙያ-ማሳደጊያ ሆኖ ስልጠናው መቅረብ አለበት።

በDCPS በመደበኛነት ልክ እንደሚፈለጉት በአንድ ዓይነት ሁኔታ በሆነ መንገድ፣ የገንዘብ እርዳታን የሚያገኙ ተቋማቶች (funded entities) እና በኤጀንሲ የተቀጠሩ የኮንትራት ሠራተኞች፤ የዲሲ በቋንቋ እገዛ ማግኛ ድንጋጌ (DC Language Access Act) መስፈርቶችን ማክበራቸውን ለማረጋገጥ፣ DCPS የሚከተሉትን ሂደቶች ይጠቀማል:

- የገንዘብ እርዳታን ለሚያገኙ ተቋማቶች (funded entities) እና የኮንትራት ሠራተኞች፣ በDCPS በቀረቡት በሁሉም፣ የገንዘብ እርዳታ መኖሩን ማስታወቂያዎች (Notices of Funding Availability (NOFA)፣ እና ፕሮፖዛል እንዲያስገቡ መጠየቂያዎች (Requests for Proposal (RFP) ውስጥ፣ በቋንቋ እገዛ ማግኛ ተገዢነት መስፈርቶችን ማካተት፤
- በኮንትራቶች ውስጥ፣ የስምምነት ማስታወሻዎች (memorandums of agreement (MOA)፣ ወይም የገንዘብ እርዳታን በሚያገኙ ተቋማቶች (funded entities)/የኮንትራት ሠራተኞች መካከል የተፈረሙ የስራ ስምምነቶች ውስጥ፣ ሁሉም የገንዘብ እርዳታን የሚያገኙ ተቋማቶች (funded entities) እና የኮንትራት ሠራተኞች የቋንቋ እገዛ ማግኛ ተገዢነት መስፈርቶችን፣ እንደሚያሟሉ በፅሁፍ ማረጋገጥ ያስፈልጋቸዋል፤
- የገንዘብ እርዳታን የሚያገኙ ተቋማቶች (funded entities) እና የኮንትራት ሠራተኞች፣ በDCPS አማካኝነት በቋንቋ እገዛ ማግኛ ተገዢ-የመሆን ፕሮቶኮሎች መረጃዎችን ማግኘታቸውን ማረጋገጥ፣
- ማንኛውንም ከLEP/NEP ባለድርሻ አባላት (stakeholders) ጋር ገጠመኞችን፣ ሪፖርት ማድረግንና የመረጃ-ስብስብ (data) የመሰብሰብ ግልጽ የሆነ ሂደትን ወደ ኤጀንሲው በማቅረብ ላይ እና የገንዘብ እርዳታን የሚያገኙ ተቋማቶችን (funded entities) እና የኮንትራት ሠራተኞችን ከአቅራቢ ድርጅቶች ጋር የቋንቋ እገዛ ማግኛ ተገዢነት መመሪያዎችን ለመተርጎምና ለማስተርጎም ማቅረብ።

H. በቋንቋ እገዛ ማግኛ የግንኙነት ክፍል (Points of Contact) የተሰጠ ውክልናዎች እና ኃላፊነቶች

ሁሉም የDCPS ርዕሰ መምህራኖች በቋንቋ እገዛ ማግኛ የግንኙነት ክፍል (Liaison) ሰይሞ መወከል አለበት። ፕሮቶኮሎችን፣ ዘዴዎችን፣ እና በቋንቋ እገዛ የማግኛ ድንጋጌን እና የዚህን ፖሊሲ መስፈርቶች ለማሟላት የሚያስፈልጉ ልምዶችን ለመፍጠት ሲባል፤ ከበቂ የኃላፊነት ስልጣን ጋር፣ የግንኙነት ክፍሉ (Liaison) ሚና፣ ለትምህርት ቤቱ አባል መመደብ አለበት።

ሁሉም የDCPS ምክትል-ሹሞች፣ ለእያንዳንዱ በሕዝቡ-ፊት ለሚቀርቡ ክፍሎች፣ ቡድን ወይም ጣቢያ (unit)፣ የግንኙነት ክፍል (Liaison) መመደብ ያስፈልጋቸዋል። በሕዝቡ-ፊት የሚገኝ ጣቢያ (unit)ን የዕለት-ተዕለት ክንውኖችን ለሚቆጣጠር እና በቋንቋ እገዛ ማግኛ ተገዢነት መስፈርቶች በስፋት ለማስፈጸም ስልጣን ለተሰጠው ተቀጣሪ ሠራተኛ፤ የግንኙነት ክፍል (Liaison) ሚናው መመደብ አለበት።

ሁሉም በግንኙነት ክፍል (Liaison) ተሰይመው የተወከሉ ሁሉ፣ ከDCPS በቋንቋ እገዛ ማግኛ ክፍል (Language Acquisition Division) ዋናው ዳይሬክተር ወይም ተወካዩ ጋር በመሆን፣ የዲሲ በቋንቋ እገዛ ማግኛ ድንጋጌን ለማስፈጸም መስራት ያስፈልጋቸዋል። እነዚህ ኃላፊነቶች የሚያካትቱት ለ:

- በቤተሰቦች በተደጋጋሚነት የሚዘወተሩ፣ እንደ ዋናው-ቢሮዎች እና የወላጅ ማዕከላት ባሉ ቦታዎች ላይ አስፈላጊ የሆኑ ተለጣፊ ምልክቶች (signage) በሚታይ ሁኔታ መቀመጣቸውን ማረጋገጥ፣
- የትምህርት ቤቱን/የጣቢያው (unit)ን በቋንቋ እገዛ ማግኘት ተገዢነት ጥረቶችን ያቀነባብራል፤
- ይህን ፖሊሲ በትምህርት ቤቱ/በጣቢያው (unit) ውስጥ መስፋፋቱን እና በስራ ላይ መዋሉን ያረጋግጣል፤
- ሁሉም በሕዝቡ-ፊት የሚቀርቡ ሠራተኞችን፤ አዲስ ተቀጣሪዎችን ጨምሮ፤ በየጊዜው ስልጠና መውሰዳቸውን እና ሁሉንም በቋንቋ እገዛ ማግኛ መስፈርቶች ለማክበር በሚገባ የታጠቁ መሆናቸውን ማረጋገጥ፣ እና
- ትምህርት ቤቱ የመረጃ-ስብስብ(Data)ን እና ሪፖርት ማድረጊያ መስፈርቶችን ማሟላቱን ያረጋግጣል።

I. ቅሬታዎች

ስለ ቋንቋ እገዛ ማግኘት ጥሰቶች የሕዝብ አቤቱታዎችን በተመለከተ፣ ወደ ዋናው አስተዳዳሪ/ተቆጣጣሪ እና ተገቢ የሆነውን የDCPS በቋንቋ እገዛ ማግኛ የማነጋገሪ ክፍል፤ ወዲያውኑ ሪፖርት መደረግ አለበት። ከዚያም በኋላ፣ የDCPS በቋንቋ እገዛ ማግኛ የማነጋገሪ ክፍሉ - ልክ አቤቱታውን እንደተቀበለ፤ የአቤቱታ ሪፖርቱን ወደ 'OHR' በቋንቋ እገዛ ማግኛ ዳይሬክተር ያስገባል።

አድራሻ:	ቪኪ ጃቪር (Vicki Javier)ን፣ (ወይ በኢሜል፣ በፅሁፍ፣ ወይም ደግሞ በስልክ)
ኢሜል:	vicki.de-javier@k12.dc.gov
ስልክ፡	202-868-6508 መደወል።
አድራሻ:	የቋንቋ እገዛ ማግኛ ክፍል (Language Acquisition Division (LAD)፣ 4400 Iowa Ave NW, Suite 1242 Washington, DC 20011

በተጨማሪም፣ በቋንቋ እገዛ ማግኘት ላይ አቤቱታን ማቅረብ-ለሚፈልግ ሰው፣ የ'OHR' በቋንቋ እገዛ ማግኘት አቤቱታ ቅጽ[25]ን እና የስልክ ቁጥር (202-727-4559)ን፣ የDCPS ሠራተኛው መስጠት አለበት።

V. ፖሊሲውን ለማስፈጸም የሚያስፈልጉ መስፈርቶች

ሁሉም የDCPS ተቀጣሪ ሠራተኛ እና ተዛማጅ የሆኑ ግለሰቦች፤ የበጎ-ፈቃድ ሠራተኞችን፣ የትብብር ፕሮግራም ሠራተኞች፣ የልምምድ ሠራተኞች (interns)፣ አብረው የሚሰሩ (fellows)፣ እርዳታ ሰጪዎች፣ የኮንትራት ሠራተኞች፣ ተዛማጅ ሠራተኞች፣ እና ሌሎች በቀጥታ ወይም በDCPS አማካኝነት ከሕዝቡ ጋር ግንኙነት የሚያደርጉ ተቋማትን ወይም ግለሰቦችን ጨምሮ፣ በዚህ ፖሊሲ የተቀመጠውን መስፈርቶች ውስጥ ተሳታፊ ሆነው ማክበር ያስፈልጋቸዋል። ይህን አፈፃፀም ለመደገፍ፣ ርዕሰ መምህራኖች እና ምክትል ሹሞች፤ በየ-ዓመዊነት ላይ መሠረት ባደረገ ሁኔታ፣ የሚያስፈልጉ እንቅስቃሴዎችን እና የጊዜ አቀማመጥን ለሠራተኞች እንዲያውቁት ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

የዚህ ፖሊሲ አፈፃፀም፤ በመደበኛ የመረጃ ስብስብ (data) ምልከታዎች፣ የመዝገብ ናሙናዎች፣ ከስር ያሉ ሰነዶች ላይ ምልከታ በማድረግ፣ እና ቦታዎችን መጎብኘት (እንደ አስፈላጊነቱ) - እነዚህን ሁሉ ያካተተውን፣ በማዕከላዊ የበላይ ክትትል ሂደት አማካኝነት፣ በቋንቋ እገዛ ማግኛ ክፍል (Language Access Division) ተጠናክሮ ይካሄዳል። ይህ ማዕቀፍ (framework)፣ ሁላችንም በአንድነት ቀጣይነት ያለው ማሻሻያዎችን እና አለመገዛትን-የሚከላከል ዘዴን እንድንገነባ ያረጋግጥልናል።

DCPS እያንዳንዱን ተማሪ በፍህታዊነት፣ በላቀ ሁኔታ፣ በግልጽነት፣ እና በተጠያቂነት ለማገልገል ቁርጠኝነቱን ያሳያይል። ስለ ማንኛውም ስጋቶች ወይም ይህን መመሪያ ላይ በሚደረጉ ጥሰቶች፣ የኦንላይን መምሪያ (Online Referral) ቅጽ[26]ን በመሙላት ወይም ኢሜል ወደ dcps.cio@dc.gov. በመላክ፤ የዕንባ-ጠባቂ (Ombudsman) ቢሮን (ከዚህ-ቀደም የሃቀኝነት ሹም ባለስልጣን (Chief Integrity Officer) ተብሎ ይታወቅ የነበረውን) ያነጋግሩ።

ይህ ፖሊሲ በየሁለት ዓመቱ እንደገና ምልከታ የሚደረግበት እና እንደአስፈላጊነቱ ይስተካከላል።

[25] OHR Language Access Complaint Form, *available at* https://ohr.dc.gov/page/LAportal/public.
[26] Office of the Ombudsman Online Referral Form, *available at* https://dcps.dc.gov/page/office-integrity.